# የእግዚአብሔርን ተስፋዎች መጨበጥ

ኢየሱስን ለመምሰል፣
ለሕይወትና ለፍሬያማ አገልግሎት።

ከዶክተር ዓለሙ ቢፍቱ

ይህንን
መጽሐፍ
ያለ ደራሲው
ፈቃድ ማባዛት
ወይም ማሳተም
በሕግ የተከለከለ ነው።

@Copyright Alemu Beeftu, May, 2001

All rights are reserved

# መቅድም

የዚህ መጽሐፍ አቢይ ትኩረት የእግዚአብሔርን ተስፋዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ አውጥቶ ማሳየት ነው። አንባቢው በርዕሶቹ ላይ በቃሉ ተስፋ ላይ እንዲመሠረት በማሰብ ብዙ መግለጫና ትንተናን ከመስጠት ተቆጥቤአለሁ። ይህ ባይሆን ኖሮ በእያንዳንዱ ተስፋ ላይ ራሱን የቻለ መጽሐፍ መጻፍ ባስፈለገ ነበር። የዚህ መጽሐፍ ተልዕኮ ግን አንባቢው ከእግዚአብሔር አፍ በወጣው ቃል ኪዳን ላይ ተመሥርቶ ሕይወቱን እንዲገነባ ለማበረታታት ስለሆነ ተገቢው ቅድሚያ ለመለኮታዊ ተስፋዎች ተሰጥቶአል። ተስፋዎቹን የማያውቅ ክርስቲያን በድግስ ቤት ተቀምጦ በረሃብ የሚሞትን ሰው ይመስላል። የብዙ ሰዎች ችግር የተስፋዎች እጦት ሳይሆን እንደ ጌታ ቃል መሠረት የእነርሱ የሆነውን ጠንቅቆ ያለማወቅ ስለሆነ በቃል ኪዳኑ መሠረት ተስፋዎቻችንን ጨብጠን በእምነት፤ በተስፋና በፍቅር እንኑርባቸው!

## መግቢያ

እግዚአብሔር አምላካችን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስንና መንፈስ ቅዱስን ወደ እኛ በመላክ የሰጠንን ተስፋዎች ሙሉ በሙሉ ለመረዳት ከሰው አዕምሮ ችሎታ በላይ ነው። ይህም በመሆኑ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት ተስፋዎች በበለጠ ያለንን እንድናውቅ የጌታን ቃል በመንፈስ ቅዱስ አስተማሪነት ተግተን እንድንመረምር ለማበረታታት ያህል ነው እንጂ ተስፋዎቹን ሁሉ ለመዘርዘር አይደለም።

የእግዚአብሔርን ተስፋዎች በሙሉ መዘርዘር የማይቻል ነው። በመሆኑም ለምሳሌነት የተጠቀሱትን እነዚህን ተስፋዎች ማንኛውም ክርስቲያን በጥሞና መርምሮ በሥራ ላይ ቢያውላቸው በጌታ ውስጥ ጽኑ መሠረትን ከማግኘቱም በላይ ሙላት ወደ አለው ሕይወት ይጓዛል። የእግዚአብሔር ተስፋዎች እንደ መድኃኒት ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ተጻፉ ብቻ ሊጠቅሙን አይችሉም። እንዲጠቅሙን ከፈለግን የጌታን ቃል አንብበን መመሪያውን በመከተልና የእምነት እርምጃ ወስደን ከሕይወታችን ጋር ማዋሃድ ይኖርብናል። ለዚህ ነው ጌታ ለነቢዩ ለሕዝቅኤል "ቃሉን እንዲበላ"፤ ለኢያሱ ደግሞ "ቃሉን እንዲያሰላስል"፤ ለእስራኤላውያንም "ቃሉን በእምነት ከሕይወታቸው ጋር ማዋሃድ" እንዲችሉ የነገራቸው።

መድኃኒት በዕቃ ውስጥ ሆኖ ጥሩና ንጹህ በሆነ መደርደሪያ ላይ ስለ ተቀመጠ በሽተኛውን ጠቅሞታል ማለት አይደለም። መድኃኒቱ ጥቅም እንዲሰጥ ከተፈለገ እንደ መመሪያው መሠረት መወሰድ ወይም መዋጥ አለበት። ከዚያ በኋላ ብቻ ነው የሚጠቅመው። የእግዚአብሔርም ተስፋዎች እንዲሁ ናቸው። ለዚህም ነው የሀገራችን ዘማሪ እናምናለን በመስቀሉ፤ እንቆማለን በወንጌሉ፤ ሕያው ሆኖ ይሠራል አልተለወጠም ቃሉ ብሎ የዘመረው።

ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል ካላወቀ ተስፋውን ሊረዳ አይችልም። ስለዚህ ተስፋችንን አውቀን የተስፋዎቹን ፍሬዎች መብላት ከፈለግን፤ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ቃሉን በጥሞና ማጥናት ይገባናል። የእግዚአብሔርን ተስፋዎች ስናጠናና በሕይወታችን ውስጥ በሥራ ላይ ስናውላቸው፤ በተስፋዎቹ ላይ እንዳንጨምርም እንዳንቀንስም መጠንቀቅ በጣም አስፈላጊ ነው። በተገለጹና በማያሻሙ ተስፋዎቹ ብንጠቀም፤ ሌሎቹን ጌታ በጊዜው ያሳየናል። «ምስጢሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው፤ የተገለጠው ግን

የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ እናደርግ ዘንድ ለእኛ ለዘላለምም ለልጆቻችን ነው።» (ዘዳ. 29፡29)

## ከእግዚአብሔር የሆነውንና ያልሆነውን ተስፋ እንዴት እንለያለን?

የእግዚአብሔር ተስፋዎች የተሰጡት ከእግዚአብሔር ምሕረትና ፍቅር የተነሣ ነው። ተስፋዎቹ የተሰጡትም ለእኛ በረከትና ለእርሱ ክብር እንዲሆኑ ነው። ይህም ስለሆነ የእውነተኛ ተስፋዎች ሁሉ መመዘኛ፦

1. ክርስቶስ ኢየሱስን ከሁሉ በላይ ከፍ ከፍ የሚያደርግ፤
2. የእግዚአብሔር ፈቃድ በሙላት በሕይወታችን ውስጥ እንዲፈጸም የሚያግዝ፤
3. እግዚአብሔርን የሚያስከብር መንፈሳዊ ፍሬ ማፍራት የሚያስችል፤
4. ሙላት ያለው የክርስትና ሕይወት ለመኖር የሚያበቃ፤ እና
5. ሰዎችን የሚያንጽ፤ ጌታን የማያውቁትን ወደ ወንጌል ብርሃን የሚያመጣና ጌታን በሚያስከብር ሁኔታ ማገልገልን የሚያስችለን ነው።

በምንም ዓይነት የኑሮ ደረጃ ላይ ብንገኝም እግዚአብሔር በእምነት ለሚፈልጉት የሰጠው ተስፋ ከሁሉም የሚበልጥ ነው። ይህም ማለት ከደረስንበትና ከተለማመድናቸው መንፈሳዊ ልምምዶች ሁሉ በላይ የሆነ የእግዚአብሔር በረከት በሙላት ይጠብቀናል ማለት ነው። ይህም በመሆኑ በምንም ዓይነት መንፈሳዊ ልምምድ ውስጥ ብንሆንም ገና ያልወረስነው ተስፋ አለን ማለት ይቻላል። እነዚህም ተስፋዎች እስከ አሁን ካየናቸው፤ ከጨበጥናቸው፤ ከኖርንባቸው ሁሉ በላይ የላቁ ናቸው።

ጌታን እንደ ግል አዳኝህ ብትቀበለው ወይም ብታውቀው አሁን ካለህ ኑሮ የሚበልጥ በክርስቶስ ትንሣኤ የተዘጋጀ ሕይወት ይጠብቅሃል። ይህ የሚሆነው እንደ ተስፋው ጥሪውን አክብረህ ልጁ ለመሆን ሕይወትህን ለእርሱ ከሰጠህ ነው። የጌታ ልጅ ሆነህ ይቅርታውንና ፍቅሩን እየተለማመድክ የምትኖር ከሆንክ የበለጠ የጸጋ በረከት ተዘጋጅቶልሃልና በእምነት ለመቀበል ልብህን አስፋው። በአገልግሎትም ውስጥ ሆነህ ታላቅ ሥራውን ያየህ ታማኝ ባሪያው ብትሆንም ከተለማመድከው ተስፋ የሚበልጥ በረከት ስለሚጠብቅህ በነበረህና ባለህ ልምምድ አትወሰን። ወደ ክርስቶስ ሙላት

እንድትገባ ተስፋው ለአንተ ነውና እግዚአብሔር የሰጠህን ተስፋዎቹን ለመውረስ ትጋ።

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔርን ተስፋዎች ማወቅ ለምን ይጠቅማል ትላለህ?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

2. ተስፋ ምንድን ነው?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

3. እንዴት ነው ተስፋውን የምናውቀው?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

4. የእግዚአብሔርን ተስፋ እንዴት ትገልጸዋለህ?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

5. እግዚአብሔር ሰጠኝ ብለህ የምታስበውን ተስፋ ለመዘርዘር ሞክር:-

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

ተስፋ ወደፊት ሊፈጸም የተወሰነ ውል ወይም ስምምነት ነው። ተስፋን ተስፋ የሚያደርገው የመፈጸሙ እርግጠኝነት ነው። እንደሚፈጸም እርግጠኛ ያልሆንበትን ስምምነት በተስፋ አንጠብቀውም። ይህም በመሆኑ ተስፋን ታላቅና እርግጠኛ የሚያርገው የተስፋ ሰጪው ማንነት ነው። የተሰጠውንም ተስፋ ለማመንም ሆነ ላለማመን ተስፋ የሰጠውን ሰው ጠባይ፤ ታማኝነት፤ ችሎታ፤ እውነተኛነትና አጠቃላይ የሕይወቱን ምስክርነት አረጋግጦ ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። እንዲሁም ደግሞ ለውሉ ስምምነት የተጻፉ ነገሮች ወይም ምስክሮች መኖር አለባቸው።

<u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. የእግዚአብሔርን ባሕርያት ለመዘርዘር ሞክር።

- ___
- ___
- ___
- ___
- ___

## የእግዚአብሔር ተስፋዎች እርግጠኝነት

የእግዚአብሔር ተስፋዎች ያለጥርጥር ሊፈጸሙ እንደሚችሉ ቋሚና ጽኑ ማረጋገጫ የሚሰጠን የእግዚአብሔር ቃል ነው። የእግዚአብሔርን ተስፋዎች እርግጠኛ ከሚያደርጓቸው እውነታዎች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት አሥር ነጥቦች ናቸው።

1. እግዚአብሔር እራሱ ስለ ተናገረ። እግዚአብሔር ሊዋሽ ወይም ቃሉን ሊለውጥ ስለማይችል የገባቸው ተስፋዎች ሁሉ ይፈጸማሉ። «የእስራኤል ኃይል እንደ ሰው የሚጸጸት አይደለምና አይዋሽም አይጸጸትም አለው።» (1ሳሙ. 15፡29)

2. የእግዚአብሔር ተስፋዎች ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉ ስለሆኑ ጸንተው የሚቆሙ ዋልታዎች ናቸው። ምክንያቱም ቃሉ አይለወጥም። «ሰማይና ምድር ያልፋሉ፤ ቃሌ ግን አያልፍም።» (ማቴ. 24፡35)

3. እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ሁሉ ለመፈጸም ችሎታና ኃይል አለው። «ለእግዚአብሔርም ክብር እየሰጠ የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል አጥብቆ እየተረዳ በእምነት በረታ እንጂ በአለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም።» (ሮሜ 4፥21)

4. እግዚአብሔር የገባውን ተስፋ ሁሉ ጠብቋል። "እግዚአብሔርም የተናገረውን ቃል አጸና፤ እግዚአብሔርም ተስፋ እንደ ሰጠ በአባቴ በዳዊት ፋንታ ተነሣሁ፤ በእስራኤል ዙፋን ላይ ተቀመጥሁ፤ ለእስራኤልም አምላክ ለእግዚአብሔር ስም ቤት ሠራሁ።" (1 ነገ. 8፥20)

5. እግዚአብሔር የገባውን ተስፋ ለመጠበቅ አይዘገይም። "ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፤..." (2ጴጥ. 3፥9)

6. የእግዚአብሔር ተስፋዎች በዘመን ስላልተወሰኑ ለእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ የሚውሉ ናቸው። "የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችን ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና..." (ሐዋ. 2፥39)

7. የእግዚአብሔር ተስፋ ብዙ ምስክሮች ያሉት ጽኑ ቃል ኪዳን ነው። "እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን፤ እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን፤ የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፤ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና።" (ዕብ. 12፥1–2)

8. የእግዚአብሔር ተስፋዎች የተሰጡት ለጥቅማችን ስለሆነ በእምነት ልንወርሳቸውና ልንኖርባቸው እንችላለን። "የመንፈስን ተስፋ በእምነት

እንድንቀበል የአብርሃም በረከት ወደ አሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርስላቸው ዘንድ።" (ገላ. 3፥14)

9. የእግዚአብሔር ተስፋዎች የማያሳፍሩ ከመሆናቸውም በላይ መልካም ናቸው። "በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም።" (ሮሜ 5፥5)

10. የእግዚአብሔር ተስፋዎች በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የጸኑ ቃል ኪዳኖች ስለሆኑ ውድ የሆኑና ፍጹምነት ያላቸው ናቸው። "እግዚአብሔር ለሰጠው የተስፋ ቃል ሁሉ አዎን ማለት በእርሱ ነውና፤ ስለዚህ ለእግዚአብሔር ስለ ክብሩ በእኛ የሚነገረው አሜን በእርሱ ደግሞ ነው።" (1ቆሮ. 1፥20፤ 2ኛ ጴጥ. 1፥4)

ሰዎች ሁሉ እነዚህን አስተማማኝ የሆኑትን የእግዚአብሔርን ተስፋዎች ተረድተው በሥራ ላይ በማዋል ቢጠቀሙበትና በኑሮአቸው ውስጥ ዕለት በዕለት ቢለማመዱት የግል ሕይወታቸውን ለማሳደግም ሆነ ፍሬያማ አገልግሎት ለማበርከት ይጠቅማቸዋል።

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ከላይ ለተዘረዘሩት ለእያንዳንዱ ነጥብ ተጨማሪ ጥቅስ ወይም ምሳሌዎች ፈልግ?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

2. እነዚህን ተስፋዎች ማወቅ እንዴት ይጠቅማል?

- ______
- ______
- ______
- ______

## ለእኛ የተሰጡ የእግዚአብሔር ተስፋዎች አጠቃላይ ዝርዝር

እግዚአብሔር ለሰዎች ልጆች የሰጣቸውን ተስፋዎች በአምስት ክፍሎች ክፍሎ መመልከት ይቻላል።

የመጀመሪያው፤ ለኃጢአተኞች ሁሉ የተሰጠ የደህንነት ወይም የሕይወት ጥሪ ተስፋ ነው።


ሁለተኛው፤ ከደህንነት ጋር የተሰጡን ወይም አንድ ሰው ጌታን በተቀበለ ጊዜ ወዲያውኑ በሕይወቱ ውስጥ የሚፈጸሙ ተስፋዎች ናቸው።

ሦስተኛው፤ ሰው ጌታን ከተቀበለ ጊዜ ጀምሮ አምላኩን እስከሚገናኝ ድረስ በክርስትና ሕይወቱ ውስጥ የሚፈጸሙ ተስፋዎች ናቸው።

አራተኛው፤ ለተለያዩ ሰዎች በተለያዩ ጊዜያትና ሁኔታዎች የተሰጡ ተስፋዎች ሲሆኑ፤

አምስተኛው፤ ገና ዓይን ያላያቸውና በጌታ ዳግም መምጣት ለእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ ሊሰጡ የተዘጋጁ ተስፋዎች ናቸው። የደህንነትም ጥሪ ሆነ ጌታን በተቀበልን ጊዜ በሕይወታችን ውስጥ የሚፈጸሙ ተስፋዎች፤ በክርስትና ሕይወታችንም ውስጥ ጌታ ዕለት በዕለት የሚያደርገውና ከዚህ ሕይወት በኋላ ለተዘጋጀልን ታላቅ መዳን መሠረቱ የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ነው። ያለ ክርስቶስ መስቀል ሕይወትንም ሆነ መንፈሳዊ በረከትን መቀበል አይቻልም። ኢየሱስም፦ «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ ከእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።» ያለው ለዚሁ ነውና። (ዮሐ. 14፡6)

በክርስቶስ መስቀል አማካይነት የተሰጡ የእግዚአብሔር ተስፋዎች ብዙ ቢሆኑም በሚከተሉት ዋና ዋና ሃሳቦች ሊጠቃለሉ ይችላሉ።




እነዚህን ተስፋዎች በግልጥ ማወቅ በእግዚአብሔር ለሚያምኑት ሁሉ ታላቅ ዋጋ ስላለውና ከመረዳትም በላይ ስለሆነ ስለ ተሰጣቸው ደኅንነት ጌታን ከልባቸው እንዲያመሰግኑት፤ እንዲያመልኩትና እንዲያገለግሉት ያደርጋቸዋል። በተጨማሪም የተፈጸሙ ተስፋዎችን ማወቃቸው በተሰጣቸው ተስፋ ተጠቅመው የድልንና ፍሬያማን ኑሮ እንዲኖሩ ያስችላቸዋል። በመጨረሻም የሚጠብቃቸውን ተስፋ መረዳታቸው የጌታን መገለጥ በናፍቆት ሲጠባበቁ በጊዜያዊ የፈተና ማዕበል ውስጥ ጸንተው ለመቆም ድፍረትን

ይሰጣቸዋል። «ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ስቃይ ምንም እንዳይደል አስባለሁ። (ሮሜ 8፥18)

ከላይ ለመጠቃቀስ የተሞከሩትን የእግዚአብሔርን ተስፋዎች ዘርዘር አድርገን ስንመለከታቸው የሚከተሉትን ይመስላሉ፤

## 1. ላልዳኑት የተሰጠ ተስፋ

1. የደህንነት ጥሪ ተስፋ

## 2. ጌታን ለሚቀበሉ የተሰጡ ተስፋዎች

2.1 የእግዚአብሔር ልጅ ሆነሃል።
2.2 የዘላለም ሕይወት ተሰጥቶሃል።
2.3 የኃጢያት ይቅርታ ተሰጥቶሃል።
2.4 አዲስ ፍጥረት ሆነሃል።
2.5 ስምህ በሕይወት መጽሐፍ ተጽፎአል።
2.6 በመንፈስ ቅዱስ ማህተም ታትመሃል።
2.7 እግዚአብሔር አባት ሆኖልሃል።
2.8 ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግረሃል።
2.9 ለኃጢያት ሞተህ ለጽድቅ ተነስተሃል።
2.10 የመዳን ልብስ አልብሶሃል።
2.11 ክርስቶስን ለብሰሃል።
2.12 ሕይወትህ በክርስቶስ ውስጥ ተሰውሮአል።
2.13 ወደ ክርስቶስ አካል ተጠምቀሃል።
2.14 እግዚአብሔር መርጦሃል።
2.15 የእግዚአብሔር ቤተሰብ ሆነሃል።
2.16 የሚማልድልህ ሊቀ ካህን አለህ።
2.17 አጽናኝ አለህ።
2.18 በክርስቶስ የክብሩ ወራሽ ሆነሃል።
2.19 እግዚአብሔር ወዶሃል።
2.20 ከመለኮታዊ ባህርይ ተካፋይ ሆነሃል።
2.21 ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን አምጥቶሃል።
2.22 ምሕረቱን ተቀብለሃል።
2.23 በመንፈሳዊ በረከቶች ሁሉ ባርኮሃል።
2.24 መንፈሳዊ ሥልጣን ተሰጥቶሃል።
2.25 የእግዚአብሔር የጦር ዕቃ ተሰጥቶሃል።

2.26 ከክርስቶስ ጋር በሰማያዊ ሥፍራ አስቀምጦሃል።
2.27 ከጨለማ ሥልጣን አድኖሃል።
2.28 የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ሆነሃል።
2.29 የክርስቶስ ፍቅር በመንፈስ ቅዱስ በልብህ ፈሶአል።
2.30 ድንጋዩን ልብ አውጥቶ የሥጋን ልብ ሰጥቶሃል።
2.31 ዓለም የማትሰጠውን ሰላሙን ሰጥቶሃል።
2.32 የነፍስ ዕረፍት ሰጥቶሃል።
2.33 ጸድቀሃል።
2.34 ተቀድሰሃል (ቅዱስ ሆነሃል)።
2.35 ክርስቶስን እንድትመስል ወስኖሃል።
2.36 የክርስቶስ ክብር ማንጸባረቂያ ሆነሃል።
2.37 እግዚአብሔር በአንተ ደስ ብሎታል።

## 3. ለክርስቲያን ሁሉ የተሰጡ ተስፋዎች

3.1 የዓለም ጨው ሆነሃል።
3.2 በክርስቶስ ከአሸናፊዎች በላይ ሆነሃል።
3.3 የክርስቶስ መልዕክተኛ ሆነሃል።
3.4 መልካም እረኛ አለህ።
3.5 የማይተኛ ጠባቂ አለህ።
3.6 እግዚአብሔር መሪ ሆኖልሃል።
3.7 ጸሎትህ የሚሰማልህና የሚመለስልህ ሆነሃል።
3.8 ጌታ ድምጹን ያሰማሃል።
3.9 ከፍቅሩ የሚለይህ የለም።
3.10 ሁሉንም ለመልካም ያደርግልሃል።
3.11 የጌታ ደስታ የአንተ ነው።
3.12 የመንፈስ ነጻነት ተሰጥቶሃል።
3.13 ጌታ ከጭንቀት ነጻ አድርጎሃል።
3.14 ከአቅምህ በላይ እንድትፈተን አይፈቅድም።
3.15 ከፈተና ሁሉ የምታመልጥበትን መውጫ ሰጥቶሃል።
3.16 ጌታ የሚያስፈልግህን ሁሉ ይሰጥሃል።
3.17 በኃይልና በድፍረት እንድትኖር ተጠርተሃል።
3.18 የተሳካ ሕይወት ተሰጥቶሃል።
3.19 ጌታ ፈዋሽህ ሆኖአል።
3.20 ለፍሬያማ አገልግሎት ተሹመሃል።
3.21 ጥበብን ይሰጥሃል።

3.22 ጌታ ለዘላለም አይለይህም።
3.23 በዓለም ካለው ይልቅ በአንተ ያለው ይበልጣል።
3.24 የክብር ንጉሥ ካህን ሆነሃል።
3.25 ከክብር ወደ ክብር ትለወጣለህ።

## 4. ስለ ቃሉ የተሰጡ ተስፋዎች

4.1 በቃሉ ሙላት እንድትኖር ተሰጥቶሃል።
4.2 የቃሉ ሰይፍ የተሰጠህ የጌታ ወታደር ነህ።
4.3 የቃሉ መዶሻ የተሰጠህ ግንበኛ ነህ።
4.4 የሚያጠራ የቃሉ እሳት ተሰጥቶሃል።
4.5 የሚያነጻ የቃሉ ውኃ ተሰጥቶሃል።
4.6 ሕይወትህን የሚያሳይ የቃሉ መስተዋት ተሰጥቶሃል።
4.7 የሚያጠግብ የቃሉ እንጀራ ተሰጥቶሃል።
4.8 የሚመራ የቃሉ ብርሃን ተሰጥቶሃል።

## 5. ስለ መንፈስ ቅዱስ የተሰጡ ተስፋዎች

5.1 በመንፈስ ቅዱስ ሕይወት ተሰጥቶሃል።
5.2 የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ተሰጥቶሃል።
5.3 የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሰጥቶሃል።
5.4 የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ተሰጥቶሃል።
5.5 የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ተሰጥተውሃል።
5.6 የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ተሰጥተውሃል።
5.7 ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኘው ቅድስና ተሰጥቶሃል።
5.8 የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ተሰጥቶሃል።
5.9 የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት አለህ።
5.10 መንፈስ ቅዱስ ያስተምርሃል።
5.11 መንፈስ ቅዱስ ይጸልይልሃል (ይማልድልሃል)።

## 6. ለተለያዩ ሰዎችና ሁኔታዎች የተሰጡ ተስፋዎች

6.1 አባት ለሌላቸው አባት እንደሚሆናቸው ተስፋ ሰጥቷል።

## 7. ለመበለቶች

7.1 ይፈርድላቸዋል።

8. ለድሆች

8.1 መጠጊያ ይሆናል።

9. ለመጻተኞችና ለስደተኞች

9.1 ይጠነቀቅላቸዋል።

10. እግዚአብሔርን ለሚፈሩ የተሰጡ ተስፋዎች

10.1 ለሚፈሩት ጥበብን ይሰጣቸዋል።
10.2 ለሚፈሩት ረዥም ዕድሜን ይሰጣቸዋል።
10.3 ለሚፈሩት የሕይወት ምንጭ ይሰጣቸዋል።
10.4 የሚፈሩትን ያስተምራቸዋል።
10.5 የሚፈሩት በሥራቸው ይባረካሉ።
10.6 የሚፈሩት በሕይወታቸው ይባረካሉ።
10.7 የሚፈሩት ቤተሰባቸው ይባረካል።
10.8 የሚፈሩትን ይጠብቃቸዋል።
10.9 ለሚፈሩት ምሕረቱን ያበዛላቸዋል።

11. ለጻድቃን የተሰጡ ተስፋዎች

11.1 የእግዚአብሔር ዓይኖች በጻድቃን ላይ ናቸው።
11.2 ጻድቃንን አይተዋቸውም።
11.3 ለጻድቃን መሸሸጊያቸው ይሆናል።
11.4 ለጻድቃን መንገዳቸውን ያበራል።
11.5 ለጻድቃን ኃይላቸውን ያበዛል።
11.6 ጻድቃን አይራቡም።
11.7 ጻድቃን መልካም ነገር አይጎድልባቸውም።

12. እግዚአብሔርን ለሚሰሙት የተሰጠ ተስፋ

12.1 ያለ ስጋት ይኖራሉ።

13. እግዚአብሔርን ለሚጠባበቁት የተሰጡ ተስፋዎች

13.1 የሚጠባበቁት አያፍሩም።
13.2 የሚጠባበቁት ኃይላቸውን ያድሳሉ።
13.3 የሚጠባበቁትን ይሰማቸዋል።
13.4 ለሚጠባበቁት ይራራላቸዋልና ብፁዓን ናቸው።

13.5 የሚጠባበቁት ደስ ይላቸዋል።

## 14. እግዚአብሔርን ለሚፈልጉት የተሰጡ ተስፋዎች

14.1 በነፍሳቸውና በልባቸው ከፈለጉት ያገኙታል።
14.2 የሚፈልጉት ይጸናሉ።
14.3 የሚፈልጉት ሥራቸው ይቃናላቸዋል።
14.4 ለሚፈልጉት ታላቅን ነገር ያደርጋል።
14.5 የሚፈልጉትን አይተዋቸውም።
14.6 የሚፈልጉትን ከመከራቸው ያድናቸዋል።
14.7 የሚፈልጉት መልካም ነገርን ሁሉ አያጡም።
14.8 የሚፈልጉትን ጌታ ይሰማቸዋል።
14.9 የሚፈልጉት ማስተዋል አላቸው።
14.10 የሚፈልጉት በሕይወት ይኖራሉ።
14.11 ለሚፈልጉት ይገኝላቸዋል።

## 15. ለሚያምኑት የተሰጡ ተስፋዎች

15.1 ለሚያምኑት ያልተወሰነ የጌታ ኃይል ይሰጣቸዋል።
15.2 የሚያምኑት የጸሎት መልስ ያገኛሉ።
15.3 ለሚያምኑት የሕይወት ዕንቅፋቶች ይነሣሉ።
15.4 የሚያምኑት እርካታ አላቸው።
15.5 የሚያምኑት የአገልግሎት ኃይል አላቸው።

## 16. ራሳቸውን ዝቅ ለሚያደርጉት

16.1 ጌታ ከፍ ያደርጋቸዋል።

## 17. ለቸሮች የተሰጡ ተስፋዎች

17.1 ቸሮች ከመከራ ይድናሉ።
17.2 ቸሮች በረከት ያገኛሉ።
17.3 ቸሮች ብልጽግና ይቀበላሉ።
17.4 ቸሮች ፍጹም ተስፋ ይኖራቸዋል።
17.5 ቸሮች የተትረፈረፈ በረከት ያገኛሉ።

## 18. በንስሐ ለሚመለሱት የተሰጡ ተስፋዎች

18.1 በንስሐ የሚመለሱትን ያድናቸዋል።
18.2 በንስሐ የሚመለሱትን ይፈውሳቸዋል።
18.3 በንስሐ ለሚመለሱት ይራራላቸዋል።
18.4 በንስሐ የሚመለሱትን ይቅር ይላቸዋል።
18.5 በንስሐ የሚመለሱት መንፈስ ቅዱስ ይቀበላሉ።
18.6 በንስሐ የሚመለሱትን የመታደስ ጊዜ ይሰጣቸዋል።

## 19. እርሱን ለሚያገለግሉ የተሰጡ ተስፋዎች

19.1 የሚያገለግሉት እንደ ሰማይ ከዋክብት ይደምቃሉ።
19.2 የሚያገለግሉት ይሸለማሉ።

## 20. ክርስቲያኖችን የሚጠብቁ ተስፋዎች

20.1 ጌታ ተመልሶ ይመጣልሃል።
20.2 የተባረከ ተስፋ ይጠብቅሃል።
20.3 አንድ ቀን በዓይን ቅጽበት ትለወጣለህ።
20.4 በአየር ጌታን ለመቀበል ትነጠቃለህ።
20.5 የሕይወት ትንሣኤ ይጠብቅሃል።
20.6 የትንሣኤን ሥጋ ትለብሳለህ።
20.7 ጌታህን ፊት ለፊት ታየዋለህ።
20.8 ጌታን ወደ መምሰል ትለወጣለህ።
20.9 በእጅ ያልተሠራ ቤት ይጠብቅሃል።
20.10 የመንግሥቱ ወራሽ ትሆናለህ።
20.11 ተወዳዳሪ የሌለው ነገር ተዘጋጅቶልሃል።
20.12 አዲስ ስም የተቀረጸለት ነጭ ድንጋይ ይሰጥሃል።
20.13 ለበጉ ሠርግ ታድመሃል።
20.14 የለቅሶና የዋይታ ዘመንህ ያበቃል።
20.15 እግዚአብሔር ለዘላለም አምላክህና አባትህ ይሆናል።
20.16 የአገልግሎት ሽልማት ተዘጋጅቶልሃል።
20.17 አሕዛብን ትገዛለህ።
20.18 በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ትኖራለህ።
20.19 ከጌታ ጋር ትነግሣለህ።
20.20 ጌታ ሁሉንም አዲስ ያደርጋል።

**20.21** የጌታን አዲስ ስም ትቀበላለህ።
**20.22** አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርን ትወርሳለህ።
**20.23** ከጌታ ጋር ለዘላለም በክብር ትኖራለህ።

"በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል ያጸናችሁማል፤ ያበረታችሁማል። ለእርሱ ክብርና ኃይል እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን፤ አሜን።" (1ጴጥ. 5፡10-11)

# ክ ፍ ል – አ ን ድ

## ለሰዎች ሁሉ የተሰጠ የእግዚአብሔር ተስፋ

ቀዳሚው የእግዚአብሔር ተስፋ የደህንነት ጥሪ ነው። ይህ ተስፋ የተሰጠው በመልኩና እንደ አምሳሉ ለፈጠራቸው ለአዳምና ለሔዋን ልጆች ሁሉ ነው። ከአዳም ኃጢአት ወይም መውደቅ ጀምሮ ከተስፋዎች ሁሉ በፊት የሚቀድመው ተስፋ ለደህንነት የሚያበቃ የንስሐ ጥሪ ነው። ይህ ጥሪ በኃጢያት ምክንያት የተቋረጠውን አንድነት በክርስቶስ ማለትም በሁለተኛው አዳም መልሶ ለመመሥረት ነው። (ሮሜ 5፡18–21) ስለዚህ የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ተስፋ የሰዎች ልጆች ሁሉ ንስሐ ገብተው በእምነት ወደ እርሱ ከመጡ በኋላ ለዘላለማዊ ሕይወት የሚያበቃቸውን የኃጢአት ይቅርታ እንደሚያገኙ የሚያረጋግጥ ነው።

"መንፈሱና ሙሽራይቱም፦ ና ይላሉ። የሚሰማም፦ ና ይበል። የተጠማም ይምጣ፤ የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ።" (ራዕ. 22፡17)

"እናንተ የተጠማችሁ ሁሉ፤ ወደ ውኃ ኑ፤ ገንዘብም የሌላችሁ ኑ ግዙ ብሉም፤ ኑ ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም የወይን ጠጅና ወተት ግዙ። ...እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት፤ ቀርቦም ሳለ ጥሩት፤ ክፉ ሰው መንገዱን በደለኛም አሳቡን ይተው ወደ እግዚአብሔርም ይመለስ እርሱም ይምረዋል፤ ይቅርታውም ብዙ ነውና ወደ አምላካችን ይመለስ።" (ኢሳ. 55፡1፤ 6–7)

"ንስሐ ግቡ ኃጢአትም ዕንቅፋት እንዳይሆንባችሁ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ። የበደላችሁትን በደል ሁሉ ከእናንተ ጣሉ አዲስ ልብና አዲስ መንፈስም ለእናንተ አድርጉ፤ የእስራኤል ቤት ሆይ ስለምን ትሞታላችሁ? የምዋቹን ሞት አልፈቅድምና ይላል እግዚአብሔር፣ ስለዚህ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ።" (ሕዝ. 18፡30–32)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. "ሰዎች ሁሉ" የሚለው ገለጻ የሚያጠቃልለው እነማንን ነው?

- 
- 
- 
- 
- 

2. የሰው ልጆች ከሌሎች ፍጥረታት ተለይተው የሚታወቁበትን ነገሮች ለመዘርዘር ሞክር። (ለምሳሌ ቋንቋ፣ መልክ፣ ትምህርት ወዘተ)

- 
- 
- 
- 
- 

3. ለእነዚህ ሁሉ እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ የደህንነት ጥሪ ነው። የደህነት ጥሪ ምንድነው?

- 
- 
- 
- 
- 

4. ማን ነው ወደ ደህንነት የሚጠራው?

- 
- 
- 
- 
- 

5. ሌሎችን ተስፋዎች ለመፈጸም ጌታ ለምን በደህንነት ጥሪ ይጀምራል?

- 
- 
- 
- 
- 

6. እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ወደዚህ ተስፋ እንዲመጡ በምን በምን መንገዶች ነው የሚጠራቸው?

- ◆
- ◆
- ◆
- ◆
- ◆

## 6.1 ባደረገላቸው ነገር አማካይነት

ከሁሉም በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ውለታ ሰውን በራሱ መልክና አምሳል መፍጠሩ ነው። «እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር የባህር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፤ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፣ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ።» (ዘፍ. 1፡26) ይህ ማለት ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ስለተፈጠረ የተወሰነ ሥልጣንና መብት እንዳለው የሚያረጋግጥ ነው።

### የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ለአንተ በግልህ የሰጠህን ችሎታ ዘርዝር?

- ◆
- ◆
- ◆
- ◆
- ◆

2. ለአምላክህ የምስጋና ደብዳቤ ጻፍለት፤

- ◆
- ◆
- ◆
- ◆
- ◆

6.1.1 <u>የማሰብና የማስተዋል ችሎታ አለው፤</u> ይህ ለሰው ሁሉ የተሰጠ ችሎታ ነው። ሰዎች በዚህ ችሎታ ተጠቅመው ወደ እርሱ ሊቀርቡና እርሱን ሊፈልጉ ይችላሉ። ካልሆነም በዚሁ ችሎታ ተጠቅመው ከእርሱም ሊርቁ

ይችላሉ። ጌታን የማይከተሉ ሊቃውንት ሁሉ እንኳ ቢሆኑ ችሎታቸውን የተቀበሉት ከእግዚአብሔር ነው።

6.1.2 <u>ምርጫ የማድረግ ችሎታ አለው፤</u> የሰው ልጅ ምርጫ የማድረግን ችሎታ የተጎናጸፈው በትምህርት ሳይሆን በእግዚአብሔር አምሳል ስለተፈጠረ የተሰጠው ስጦታ ነው። ስለዚህ ሰው ስለ ዛሬው ብቻ ሳይሆን ስለ ወደፊትም ግቡ ምርጫ የማድረግ ችሎታ አለው። የጌታ ፈቃድ ሰዎች ሁሉ የዘላለም ሕይወትን እንዲመርጡ ነው። «በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን፤ በረከትንና መርገምንም እንዳስቀመጥሁ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰክራለሁ፤ እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ፤ እግዚአብሔርም ለአባቶችህ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም እንዲሰጣቸው በማለላቸው በምድራቱም ትቀመጥ ዘንድ እርሱ ሕይወትህ የዘመንህም ርዝመት ነውና አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድደው፤ ትጠባበቀውም፤ ቃሉንም ትሰማ ዘንድ ምረጥ።» (ዘዳ. 30፡19–20)

## <u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. የምርጫ ጥቅም ምንድን ነው ለምንስ ይረዳል?

◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________

2. ምርጫ የሌለውን ሰው ምን ትለዋለህ?

◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________

6.1.3 <u>ውሳኔ የማድረግ ችሎታ አለው፤</u> ሰው ስለ ኑሮው፤ ስለ ሕይወቱና ስለ አካባቢው ብቻ ሳይሆን ስለ መንፈሳዊ ሕይወቱ ማለትም ከእግዚአብሔር ጋር እንዲኖረው ስለሚፈልገው ነገር መወሰን ይችላል። ይህም በመሆኑ

አንዳንዶች በዚህ ውሳኔ ተጠቅመው ወደ እግዚአብሔር ሲቀርቡ ሌሎች ግን በራሳቸው ምርጫ ምክንያት ከጌታ በመራቅ ራሳቸውን ይጎዳሉ።

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ጌታን ለመቀበል ውሳኔ ስታደርግ የረዳህ ማን ነበር?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

2. ጌታን በመቀበልህ ያየኸው ትልቁ የሕይወት ለውጥ ምንድነው?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

6.1.4 <u>ሰው ለዘላለም ይኖራል</u>፤ ይህም ማለት ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ስለ ተፈጠረ በጊዜ የተወሰነ ሳይሆን ዘላለማዊ ነው ማለት ነው። ስለዚህ ጥያቄው ሰው ለዘላለም መኖሩ ላይ ሳይሆን ዘላለምን የት እንደሚኖር መምረጡ ላይ ነው። ይህን ውሳኔ ለራሱ የሚወስነው እያንዳንዱ ግለሰብ ራሱ ነው። የእግዚአብሔርን አብይና ቀዳሚ ጥሪ ተቀብሎ ኅብረቱን ከጌታ ጋር ካስተካከለ ከእግዚአብሔር ጋር በመንግሥተ ሰማያት ለዘላለም የደስታን ኑሮ ይኖራል። በምርጫው ተጠቅሞ ጥሪውን ካቃለለ ግን ዕድሉ ለሰይጣንና ለተከታዮቹ በተዘጋጀው በዘላለም እሳት ውስጥ ይሆናል፤ "ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ፣ የርኩሳንም፤ የነፍሰ ገዳዮችም፤ የሴሰኞዎችም፤ የአስማተኞዎችም፤ ጣዖትንም የሚያመልኩ፤ የሐሰተኞዎችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ሁለተኛው ሞት ነው።" (ራዕ. 21፥8) ተብሎ ተጽፏልና።

<u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. ስለ ዘላለማዊ ኑሮህ ምን ያህል ታመሰግነዋለህ?

♦ ______________________________
♦ ______________________________
♦ ______________________________
♦ ______________________________
♦ ______________________________

2. የመዳን ደስታ ሊጠፋ የሚችለው በምን ምክንያት ነው?

♦ ______________________________
♦ ______________________________
♦ ______________________________
♦ ______________________________
♦ ______________________________

3. የምስጋናንና የእውነተኛ ደስታን ግንኙነት እንዴት ትገልጸዋለህ?

♦ ______________________________
♦ ______________________________
♦ ______________________________
♦ ______________________________
♦ ______________________________

6.1.5 <u>ሰው ነፍስና ሥጋ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊም ነው፤</u> (1ተሰ. 5፡23) ከዚህም የተነሣ ሥጋው ቢሞት ነፍሱ ለዘላለም ስለምትኖር አትሞትም። አንድ ቀን ሙታን የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምተው ለፍርድ በዙፋኑ ፊት የሚቆሙበት ጊዜ ይመጣል።

6.1.6 <u>ሰው የመውደድ ችሎታ አለው፤</u> እግዚአብሔር ፍቅር ነው። ሰው በእርሱ አምሳል ስለ ተፈጠረ የመውደድ ችሎታ አለው። ስለዚህ ለሰዎች እግዚአብሔርን እንዲወድዱ ጥሪ የተላለፈላቸው የመውደድ ችሎታ ስለ ተሰጣቸው ነው። "አምላካችን አንድ ጌታ ነው አንተም በፍጹም ልብህ፤ በፍጹምም ነፍስህ፤ በፍጹምም አሳብህ፤ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት። ፊተኛይቱ ትዕዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም፦ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የምትል እርስዋን የምትመስል ይህች ናት።" (ማር. 12፡30–31)

6.1.7 ሰው እግዚአብሔርን ለማወቅ የሚያስችለው ሕሊና አለው፤ "እውነትን በዓመጻ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዓመጻቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጣልና፤ እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው፤ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና።" (ሮሜ 1፥18–19)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ነፍስ ስንል ምን ማለታችን ነው?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

2. የመንፈስና የነፍስ ልዩነትና ተመሳሳይነት ምንድነው?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

3. ስሜትስ ከእነዚህ ጋር ምን ግንኙነት አለው?

- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______
- ◆ ______

## 6.2. በሚያደርግላቸው ነገሮች አማካይነት

እግዚአብሔር ዕለት በዕለት ለሰዎች ልጆች በሚያደርጋቸው ነገሮች አማካይነት ወደ ተስፋው እንዲመጡ ዕድልን ይሰጣቸዋል። ከእነዚህ ውስጥ ሁለቱን ለምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፤

6.2.1 ለጋስነቱ፦ የሰው ልጆች ለኑሮአቸው የሚያስፈልጋቸውን እንደ ከፋታቸው ሳይሆን እንደ ምህረቱ ብዛት የሚሰጣቸው እርሱ ነው። "እርሱ

በከፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፤ በጻድቃንና በኃጢያተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና።” (ማቴ. 5፥45) የሚበሉትና የሚጠጡት ብቻ ሳይሆን የሚተነፍሱትንም አየር እንኳ በነፃ ከእግዚአብሔር ነው የተሰጣቸው። ይህን ሲያደርግላቸው በቸርነቱ አማካይነት ወደ እርሱ ቀርበው እንደ አምላክነቱ እንዲያውቁትና የዘላለምንም ሕይወት እንዲያገኙ ነው።

6.2.2 ትዕግሥቱና ምህረቱ፦ እንደ እግዚአብሔር ቅድስና ቢሆን ኖሮ ኃጢአተኛ በምድር ላይ አንድ ቀንም ባልዋለም ነበር። እግዚአብሔር የሚያጠፋ እሳት ነውና። “አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነውና።” (ዕብ. 12፥29) ነገር ግን እግዚአብሔር በትዕግሥት ለሰዎች የንስሐን ዕድል ይሰጣቸዋል። “ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን?” (ሮሜ 2፥4) የክርስቶስ መምጣት እስከ አሁን ያዘገየው ለዚሁ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ሲመሰክር እንዲህ ይላል። “በሰላም በእርሱ እንድትገኙ ትጉ የጌታችንም ትዕግሥት መዳናችሁ እንደሆነ ቁጠሩ።” (2ጴጥ. 3፥15)

## <u>የውይይት</u> መነሻ ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር ልግስና እንዴት ይገለጻል?

- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______

2. ስለ እግዚአብሔር ትዕግስት ከሕይወትህ ምን ምሳሌ ትሰጣለህ?

- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______

3. ለየት ባለ ሁኔታ ምህረቱን ያስተዋልክበትን ጊዜያት ለመዘርዘር ሞክር?

- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______
- ♦ ______

## 6.3. በፍቅሩ በከፈተው የደህንነት መንገድ

እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ሰው ወደ ዘላለማዊ ተስፋ ለማምጣት የሰጠው ማስተዋልና መምረጥ የሚያስችል አዕምሮ ብቻ አይደለም። ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን አሳልፎ በመስጠትም የኃጢአት ዕዳ ስለ ከፈለ ለሰው ሁሉ በፍቅር ለሕይወት እየጠራው ነው። ቃሉም ስለዚህ ሲመሰክር እንዲህ ይላል፦ "እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቷልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል።" (1ዮሐ. 3፡16) በመንፈሳዊ ሞት ምክንያት (ኤፌ. 2፡1-2) ከእግዚአብሔር ለተለዩት የሚያስፈልገው ሕይወት ስለሆነ እግዚአብሔር ከምህረቱ የተነሣ በክርስቶስ የሕይወትን መንገድ አዘጋጅቶ ሰዎችን ሁሉ በፍቅሩ ወደዚህ ተስፋ እየጠራ ነው። ይህን የፍቅር ጥሪ ለተቀበሉት ሁሉ የእግዚአብሔር ተስፋ የኃጢያት ይቅርታና የዘላለም ሕይወት ነው። "ይህን ተስፋ ለመቀበል ከተጠሪው የሚጠበቀው ምንድን ነው?" የሚለው ጥያቄ መሠረታዊ ከመሆኑም በላይ በተለያዩ ሰዎች በልዩ ልዩ ጊዜና ቦታም የሚጠየቅ ስለሆነ በአጭሩም ቢሆን በሚከተሉት አንቀጾች ለማየት ይሞከራል። ከዘላለማዊው የእግዚአብሔር ተስፋ ተካፋይ መሆን የሚሻ ሰው ሁሉ የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ ይጠበቅበታል።

### 6.3.1 የእግዚአብሔር ቃል ስለ ሰው የሚመሰክረውን ምስክር አምኖ መቀበል አለበት።

#### 6.3.1.1 የጌታ ቃል ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ መሆኑን ይመሰክራል።

"ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉም ተሳስተዋል፤ በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል።" (ሮሜ 3፡11-12) "ሁሉም ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል።" (ሮሜ 3፡23)

#### 6.3.1.2 መጽሐፍ ቅዱስ ሰው በኃጢያቱ ምክንያት መንፈሳዊ ሕይወቱ ከመሞቱም በላይ የዘላለም ፍርድ እንዳለበት ይመሰክራል።

"በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ በእነርሱም በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው ፈቃድ በፊት ተመላለሳችሁባቸው።" (ኤፌ. 2፡2)

"በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።" (ዮሐ. 3፡18)። ይህ የዘላለም ፍርድ ምን ጊዜም የማያቋርጥ የዘላለም እሳት ነው። "ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ፤ የርኩሳንም፤ የነፍስ ገዳዮችም፤ የሴሰኞዎችም፣ የአስማተኞችም፤ ጣዖትንም የሚያመልኩ፤ የሐሰተኞዎችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት ባሕር ነው ይኸውም ሁለተኛ ሞት ነው።" (ራዕ. 21፡8)

"ለሰዎች አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱም በኋላ ፍርድ እንደ ተመደበባቸው፤ እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ፤ የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሠዋ በኋላ፤ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢአት ይታይላቸዋል።" (ዕብ. 9፡27)

"ወጥተውም በእኔ ያመፁብኝን ሰዎች ሬሳቸውን ያያሉ፤ ትላቸው አይሞትምና እሳታቸውም አይጠፋምና፤ ለሥጋ ለባሽም ሁሉ አስጸያፊ ነገር ይሆናሉ።" (ኢሳ. 66፡24)

6.3.1.3 መጽሐፍ ቅዱስ ሰው ራሱን ለማዳን እንደማይችል በግልጽ ይናገራል። "መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች የለምና።" (ሐዋ. 4፡12)

6. 3.2 እግዚአብሔር የደህንነት መንገድ እንዳዘጋጀ ማመን አለበት።

ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ወደ ዓለም የመጣው ሰው ራሱን ለማዳን ስለማይችል ነው። "ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፤ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና።" (ዮሐ. 3፡17) "ሁላችንም እንደ ርኩስ ሰው ሆነናል፤ ጽድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው፤ ሁላችንም እንደ ቅጠል ረግፈናል፤ በደላችንም እንደ ነፋስ ወስዶናል።" (ኢሳ. 64፡6) ክርስቶስ ግን የጠፋትን ሊፈልግና ሊያድን ወደ ነፍሱን

በመስቀል ላይ በመስጠት የኃጢአትን ዋጋ በፍቅሩ ከፍሎአል። “እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ የደህንነታችንም ተግሳጽ በእርሱ ላይ ነበረ፤ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።” (ኢሳ. 53፡5–6) እንግዲህ ሰው ሁሉ በክርስቶስ ደም በመንጻት የኃጢያት ይቅርታ ሊያገኝ ይችል ዘንድ እግዚአብሔር የደህንነትን መንገድ በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ አዘጋጅቷል።

6. 3.3 ለመዳን የእግዚአብሔርን ስጦታ በእምነት መቀበል አለበት።

6.3.3.1 የክርስቶስን አዳኝነት በእምነት የግሉ አድርጎ መቀበል ያስፈልገዋል።

“ለተቀበሉት ሁሉ ግን፤ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።” (ዮሐ.1፡12)

“እነርሱም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰዎችህም ትድናላችሁ አሉት።” (ሐዋ. 16፡31)

6.3.3.2 እግዚአብሔር ክርስቶስን ከሙታን እንዳነሣው በልቡ ማመን ያስፈልገዋል። “ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤” (ሮሜ 10፡9)

6.3.3.3 በአፋም የክርስቶስን አዳኝነት ብቻ ሳይሆን ትንሣኤውንም መመስከር ይኖርበታል። “ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፋም መስክሮ ይድናልና።” (ሮሜ 10፡10)

6.3.3.4 ክርስቶስን በፈቃደኝነት ወደ ሕይወቱ መጋበዝ ይኖርበታል። “እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፤ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።” (ራዕ. 3፡20)

6.3.3.5 በአዲስ ሕይወትና በልጅነት መብቱ በእምነት መኖር መጀመር ያስፈልገዋል። "የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ።" (1ዮሐ. 5፡13)

በአጭሩ የደህንነት መንገድ የሚባለው እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ በክርስቶስ የመስቀል ሥራ ያዘጋጀው የመዳን ተስፋ ነው። የደህንነት ልምምድ የሌለው ሰው ከዚህ በኋላ የተዘረዘሩትን የእግዚአብሔርን ተስፋዎች የራሱ አድርጎ ሊጠቀምባቸው አይችልም። የደህንነት ልምምድ እግዚአብሔር ለአዳም ልጆች ላዘጋጃቸው ተስፋዎችና መንፈሳዊ በረከቶች ሁሉ መሠረታዊ ነገር ከመሆኑም በላይ ዋነኛ ቁልፍ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር ስላደረገው ነገር በእውነት ለማመስገንም ሆነ በክርስቶስ የመስቀል ሥራና በመንፈስ ቅዱስ መምጣት የእኛ የሆኑትን በረከቶች ተቀብለን ሙላት ያለውን ሕይወት ለመለማመድ የደህንነታችንን ጥልቀትና ስፋት ማወቅ አስፈላጊ ነገር ነው። እግዚአብሔር በሚመጡት የዘላለም ዘመናት ሁሉ የክብሩን ባለጠግነት ለዳኑት ሁሉ እንደሚገልጽ ሲናገር መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል "... በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለ ጠግነት ያሳይ ዘንድ ከእርሱ ጋር አስነሣን..." (ኤፌ. 2፡6)።

## <u>የውይይት መነሻ ጥያቄዎች</u>

1. የደህንነት ዋጋ በምን ይተመናል?

- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________

2. ዮሐንስ 3:16 እግዚአብሔር ለሰዎች ልጆች ሁሉ ያለውን የደህንነት ያለውን ሃሳብ በምን መንገድ ገለጸ?

- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________

3. ደህንነት የሰውን በእግዚአብሔር ዓይን ፊት መከበር እንዴት ያሳያል?

- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________

## የደህንነት ምሥጢር

የደህንነታችን ምሥጢር ሙሉ በሙሉ የምንረዳው በመንግሥተ ሰማያት ብቻ ነው። ደህንነታችን እንደ ረጅም መሰላል ስለሆነ ከታች እስከ ላይ ያለውን በአንድ ጊዜ አይተን ቁንጅናውን ሁሉ ማድነቅ ያስቸግራል። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ምሥጢር ታላቅነት ሲያስታውሰን፦ "ዓይን ያላየው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንደተጻፈ፤ እንዲህ እንናገራለን" (1ቆሮ. 2፡9) ይላል። ይህ አስደናቂው ደህንነታችን ሦስት ደረጃዎች አሉት። ከዚህ ቀጥሎ እነዚህን የደህንነታችንን ደረጃዎች ወይም ክፍሎች በአጭሩ ለመግለጽ እሞክራለሁ። ልብ እንበል፤ ደህንነታችን አንድ ነው። ነገር ግን ሦስት ክፍሎች ወይም ደረጃዎች አሉት። ሦስት ማዕዘን እንዳለው ቅርጽ ማለት ነው። ቅርጹ አንድ ቢሆንም ከሦስት አቅጣጭ ማየት ይቻላል ማለት ነው። ወይም ደግሞ ሦስት እርምጃዎች ባሉት ደረጃም ሊመሰል ይችላል። የሚከተለውን ሥዕል እንመልከት። ሰው፤ ሥጋ፣ ነፍስና መንፈስ አለው። ነገር ግን አንድ ሰው ነው። ደህንነትም እንዲሁ ነው።

# የ ደ ህ ን ነ ት ደ ረ ጃ ዎ ች

**ከጌታ ጋራ መሆን** 3

ኃጢአት በሌለበት በመሆን የከበረ ሥጋ ለብሶ መኖር።

(1ጴጥ. 1፡3–5)

2

**መቀደስ**

ከኃጢአት ኃይል መዳን

( ፊል. 2:12-13)

1

**መጽደቅ**

ከኃጢአት ውጤት መዳን

( ፊል. 2:8-9)

## 1. ከኃጢአት ውጤት መዳን -- መጽደቅ

### የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ሰው እንዴትና ከምን ይድናል?

- ______
- ______
- ______

- 
- 

2. መዳን ማለት ምን ማለት ነው?

- 
- 
- 
- 
- 

3. ጽድቅ ምንድነው?

- 
- 
- 
- 
- 

የደህንነታችን አንደኛው ደረጃ ወይም ክፍል ከኃጢአት ውጤት መዳን ነው። በምንም ስም ብንጠራው የደህንነታችን መሠረቱ እላይ እንደ ተጠቀሰው የክርስቶስ የመስቀሉ ሥራ ውጤት ነው። "ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።" (ኤፌ. 2፡8-9) ልብ ማለት የሚያስፈልጉንን ነገሮች ቀጥለን እንመለከታቸዋለን፤

1.1 ግሥ ኃላፊ ጊዜን የሚያመለክት ነው። ከኃጢያት መዳን አንድ ጊዜ ለሁል ጊዜ የሚሆን ነገር ነው። ሰው ጌታን በተቀበለ ጊዜ አዲስ ፍጥረት ስለሚሆን ዳግም ልደትን ያገኛል። በሥጋ ሁለት ጊዜ እንደማንወለድ ሁሉ በመንፈስም አንዴ ነው የምንወለደው። ይህን ልደት ከሥጋ ልደት ለመለየት መጽሐፍ ቅዱስ ዳግም ልደት ይለዋል። (ዮሐ. 3) ሰው ይህን ደህንነት በመቀበል የእግዚአብሔርም ልጅ በመሆን ወደ ሕይወት ይሻገራል። (ዮሐ. 5፡24)

1.2 ደህንነቱ የጸጋ ሥራ ነው። ጸጋ፦ እግዚአብሔር ዋጋ ከፍሎበት ለእኛ በነፃ የሰጠን ምህረቱ ወይም ሞገሱ ነው። "ነጻ ስጦታ ነው" ስንል እኛ ዋጋ አልከፈልንበትም ማለታችን ነው እንጂ ዋጋ አልተከፈለበትም ለማለት

አይደለም። ደህንነትን ለእኛ ነፃ ለማድረግ ክርስቶስ የራሱን ሕይወት ሰጥቶናል። ስለዚህ ሰው ለደህንነቱ ይህን ጸጋ ከመቀበል በስተቀር የሚያደርገው ምንም ነገር የለም።

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ሃላፊ ግዶ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው?

- 
- 
- 
- 
- 

2. ደህንነት በጸጋ ብቻ የሆነው ለምንድነው?

- 
- 
- 
- 
- 

3. የደህንነት ዋጋ ስንል ምን ማለታችን ነው?

- 
- 
- 
- 
- 

1.3 የእምነት እጅ አስፈላጊ ነው። ለመዳን እግዚአብሔር የሚሰጠውን ጸጋ መቀበል ያስፈልጋል። የዚህ ጸጋ መቀበያ እጅ እምነታችን ነው። ያለ እምነት መዳንም ሆነ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም።

1.4 ደህንነታችን የተገኘው በክርስቶስ መስቀል ነው። ክርስቶስ በመስቀል ላይ ደሙን በማፍሰሱና ሞቶ በመነሣቱ እርሱ በሠራው ሥራ እኛ ከኃጢአት ዋጋ ወይም ውጤት ማለትም ከዘላለም ሞትና ፍርድ ዳንን። "የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው።" (ሮሜ 6፡23)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. እምነት ምንድነው? (ዕብ. 6:1)

- 
- 
- 
- 
- 

2. የዘላለም ሕይወት ስንል ምን ማለታችን ነው?

- 
- 
- 
- 
- 

3. ክርስቶስ መሞት ለምን እንዲሞት አስፈለገ?

- 
- 
- 
- 
- 

1.5 የዳንነው ከኃጢአት ውጤት ነው። የኃጢአት ፍሬ ሞትን፤ ፍርድን፤ የዘላለም ቁጣን አመጣብን። ክርስቶስን በተቀበልን ጊዜ ግን ከዚህ ከኃጢአት ውጤት ነፃ በመሆን ከእግዚአብሔር ጋር አንድነትን አገኘን። ስለዚህ ነው ቃሉ፦ "እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም።" (ሮሜ 8፡1) ብሎ አዋጅን ያስተላለፈልን።

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ከኃጢአት ውጤት መዳናችን ስለ አለፈው ኑሮ ምን ያስታውሰናል?

- 
- 
- 
- 
- 

2. "አዲስ ፍጥረት" ሲል ምን ማለቱ ነው?

- ◆
- ◆
- ◆
- ◆
- ◆

3. ስለ አለፈው ኃጢአትህ ጠላት ዲያቢሎስ ሲከስህ መልስህ ምንድነው?

- ◆
- ◆
- ◆
- ◆
- ◆

እንግዲህ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሠራውን ሥራ በእምነት ተቀብሎ ከኃጢአት ውጤት መዳን ለደህንነታችን ሥርና መሠረት ነው። ኃጢአት ካመጣው መዘዝ ካልዳንን ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ሊኖረን አይችልም። ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የሚኖረን የክርስቶስን ጽድቅ ስንለበስ ብቻ ነው። "ይልቁንስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቁጣው እንድናለን።" (ሮሜ 5፡9) ይህ የደህንነት የመጀመሪያ ደረጃ ከኃጢአት መጽደቅ ይባላል። ሰው ከኃጢአት ውጤት ድኖ የዘላለም ሕይወት የሚቀበለው መቼ ነው?

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. አንተ ይህን የጸጋ ደህንነት ለመቀበል ውሳኔ ያደረግከው መቼ ነው። (ምስክርነትህን በአጭሩ ጻፍ)

- ◆
- ◆
- ◆
- ◆
- ◆
- ◆
- ◆
- ◆

2. ስለ ጌታ ኢየሱስ አዳኝነት የመሰከረልህ ሰው ማን ነበር?

- ______________________
- ______________________
- ______________________
- ______________________
- ______________________

3. ላልዳኑት መመስከር ያለብን ለምንድን ነው?

- ______________________
- ______________________
- ______________________
- ______________________
- ______________________

4. መመስከር የማን ኃላፊነት ይመስልሃል?

- ______________________
- ______________________
- ______________________
- ______________________
- ______________________

5. ለሰዎች መስክረህ ታውቃለህን? (ዳን. 12:3)

- ______________________
- ______________________
- ______________________
- ______________________
- ______________________

6. በቤተ ክርስቲያን የምስክርነት ጓድ የሚባል አገልግሎት መኖር ይገባዋልን?

- ______________________
- ______________________
- ______________________
- ______________________
- ______________________

7. የመመስከር ስጦታ አለህን? የለኝም የምትል ከሆነ ምን ማለትህ ነው?

- ______________________
- ______________________
- ______________________
- ______________________
- ______________________

8. ላልዳኑት መጸለይ የማን ኃላፊነት ነው?

♦
♦
♦
♦
♦

## 2. ከኃጢአት ኃይል መዳን

የደህንነታችን ሁለተኛው ክፍል ከኃጢአት ኃይል መዳን ነው። "ስለዚህ ወዳጆቼ ሆይ ሁል ጊዜ እንደታዘዛችሁ፤ በእናንተ ዘንድ በመኖር ብቻ ሳይሆን ይልቁን አሁን ስርቅ፤ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፤ ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና።" (ፊል. 2፥12–13 እና ኤፌ. 2፥8–9) ስናመሳክር ሁለቱ የሚጋጩ ወይም የሚቃረኑ ይመስላሉ። ሐዋሪያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች ድናችኋል ሲል ለፊልጵሲዩስ ምዕመናን ደግሞ ራሳችሁን ለማዳን ኃላፊነት አለባችሁና ትጉ የሚል ይመስላል። መልዕክቱ ትክክል ነው ሁለቱም አይቃረኑም። ልዩነቱ ግን ብዙ ሰዎች እንደሚያስቡት በፊል. 2፥12–13 የሚያስተምረው ስለ መጀመሪያ ደህንነት እርምጃ ወይም ደረጃ አይደለም። መልዕክቱ ከኃጢያት ውጤት ለዳኑት ስለሆነ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ከኃጢአት ኃይል ራሳቸውን ጠብቀው በቅድስና እንዲኖሩ ነው።

<u>እግዚአብሔር</u> ከኃጢአት <u>ውጤት እንዲያድነን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደላከው ሁሉ</u> ከኃጢአት <u>ኃይል አድኖን</u> <u>በቅድስና</u> <u>እስከ</u> <u>መጨረሻ</u> <u>እንዲጠብቀን</u> <u>መንፈስ ቅዱስን ሰጠን</u>። ከኃጢአት ውጤት መዳን አንድ ጊዜ የሚፈጸም ሲሆን ከኃጢአት ኃይል መዳን ግን በየዕለቱ የሚሆን ነገር ነው። ከኃጢአት ኃይል የምንድነው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስለሆነ በመንፈስ ቅዱስ ሙላት መኖር ያስፈልገናል። ክርስቲያኖችም ብንሆን እንኳን በራሳችን ብርታት ኃጢአትን አሸንፈን የቅድስና ኑሮ መኖር አንችልም። ይህን ለማየት ሮሜ ምዕራፍ ሰባትን ማንበብ ያስፈልጋል። ሐዋርያው ጳውሎስ የራሱን ምሳሌ በመጠቀም በሥጋ ኃይል ኃጢአትን ማሸነፍ እንደማይቻል በግልጽ ያሳያል – በምዕራፍ 7 ውስጥ በእኔነት የድል ሕይወት መኖር እንደማይቻል ካረጋገጠ በኋላ ሮሜ ምዕራፍ 8 ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ኃጢአትን

አሸንፎ መኖር እንደሚቻል በግልጽ ያሳያል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ቋንቋውን ይለውጥና "በእኔነት" ቦታ መንፈስ ቅዱስን ይተካል። ሮሜ ምዕራፍ ሰባትንና ስምንትን በጥንቃቄ ማጥናት ይህን ነገር ግልጽ ያደርገዋል።

ስለዚህ የደህንነት ሁለተኛው ገጽ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ኃጢአትን አሸንፎ ዕለት በዕለት በቅድስና ሕይወት በመኖር የክርስቶስን ክብር ማንጸባረቅ ነው። ከኃጢአት ውጤት ለመዳን የጌታን ጸጋ በእምነት እንደ ተቀበልን ሁሉ ከኃጢአትም ኃይል ለመዳን የመንፈስ ቅዱስን ሙላት በእምነት ተቀብለን በእርሱ ቁጥጥር ሥር መኖር አስፈላጊ ነው። መንፈስ ቅዱስ የመጣው ለዚሁ አገልግሎት ነው። በእርሱ ወደ ደህንነት እንደ ተጠራን የክርስትናንም ሕይወት በእርሱ ሙላት እንድንኖር ታዘናልና። "መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና።" (ኤፌ. 5፡18) ይህ የደህንነት ደረጃ ቅድስና ወይም መቀደስ ይባላል።

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምንድነው?

◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________

2. በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተሃልን?

◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________

3. በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ በልሳን በመጸለይና በሙላቱ በመኖር መካከል ልዩነት አለን? ካለ ልዩነቱ ምንድነው?

◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________
◆ ____________________

♦ ____________________

4. የቅድስና ሕይወት ምን ያህል አስፈላጊ ነው?

♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________

5. መቀደስ ማለት ምን ማለት ነው?

♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________
♦ ____________________

## 3. ወደ ፍጹም ክብር መለወጥ ወይም ኃጢአት በሌለበት ቦታ መኖር

የደህንነታችን ሦስተኛውና የመጨረሻው ክፍል ወደ ክብር መለወጥ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ደህንነታችን ደረጃዎች ሲናገር ገና ያልተገለጸና ሊመጣ ያለ የደህንነታችን ገጽ እንዳለ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፦ "ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ ለሕያው ተስፋና ለማይጠፋ፤ እድፈትም ለሌበት፤ ለማያልፍም ርስት እንደ ምሕረቱ ብዛት ሁለተኛ የወለደን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፤ ይህም ርስት በመጨረሻ ዘመን ይገለጥ ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠበቃችሁ ለእናንተ በሰማይ ቀርቶላችኋል።" (1ጴጥ. 1፥3–5) ይህ የደህንነት ደረጃ ገና ያልተገለጸ ሲሆን ዳግም ለተወለዱና በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠበቁት የተዘጋጀ ነው። በሌላ አነጋገር ቀደም ሲል የተጠቀሱትን ሁለቱን የደህንነት ደረጃዎች ለተለማመዱት ሁሉ ይህ ሦስተኛውና የመጨረሻው ደረጃ በጌታችን መገለጥ ይሰጣቸዋል። ይህ ሊገለጥ ያለው የደህንነታችን የመጨረሻው ክፍል ከዚህ ሥጋ ተለይተን የከበረ የትንሣኤ ሥጋ በምንለብስበት ጊዜ በክብር የሚሰጠን ነው። ኃጢአት በሌለበት ቦታ የክብሩ ወራሾች በመሆን ከክርስቶስ ጋር ለዘላለም መኖር ነው። ይህ

የደህንነታችን የመጨረሻ ግቡ ነው። ዛሬ ከኃጢአት ውጤት ስለዳንንና በመንፈሱ ልጆቹ ስለሆንን ተስፋችንን በድንግዝግዝ እናያለን። ነገር ግን ደህንነታችን መጨረሻ ግቡ ላይ ሲደርስ ሁሉንም በግልጽ እናያለን፤ እንረዳለንም። "ዛሬ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን።" (1ቆሮ. 13፥12 ና 1ዮሐ. 3፥2)

እንግዲህ ለአዳም ልጆች ሁሉ የተሰጠ ቀዳሚ ተስፋ ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በእምነትና በንስሐ ከመጡ የዘላለምን ሕይወት ተቀብለው ሰላምና ትርጉም ያለውን ኑሮ መኖር እንደሚችሉ ነው። የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ሰው መዳን አለበት። ለዚህ ደህንነት እግዚአብሔር አብ ልጁን በፍቅር ከመላኩም ሌላ ወደ ደህንነት እንዲመራና ከዳነም በኋላ ኃይልን እየሰጠ እንዲያቆመን መንፈስ ቅዱስን ወደ ዓለም ልኮአል። አንድ ቀን መጥቶ የእርሱ የሆኑትን ወደ ቤቱ ይወስዳቸዋል። ቀደም ሲል እንዳየነው ከኃጢአት ውጤት መዳን ወደ ቅድስና ኑሮ ይመራል። በቅድስና የሚኖር ክርስቲያን ራሱን ለኢየሱስ ክርስቶስ ጌታነት ያስገዛል፤ የጌታንም ዳግም መገለጥ በናፍቆትና በተስፋ ይጠባበቃል። ጌታውንም አንድ ቀን በክብር ያየዋል።

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ጌታ ዛሬ ቢመለስ አንተን የሚያገኝህ የት ነው?

◆ ______
◆ ______
◆ ______
◆ ______
◆ ______

2. ስለ ጌታ ዳግም መምጣት ምን ያህል ተረድተሃል?

◆ ______
◆ ______
◆ ______
◆ ______
◆ ______

3. የጌታ ዳግም ምፅአት ምልክቶች ምንድን ናቸው? (ማቴ. ማር. ሉቃ. 1ቆሮ. 15፣ 1ተሰ. አንብብ)

- 
- 
- 
- 

4. ስለ ጌታ መመለስ የሚናገሩትን መጻሕፍትና ምዕራፍ ዘርዝር።

- 
- 
- 
- 
- 

5. በሁሉም ውስጥ የተጠቀሱ ተመሳሳይ ነገሮች አሉን?


- 
- 
- 
- 
- 

6. ካሉ ምንድን ናቸው?

- 
- 
- 
- 
- 

ይህንን የደህንነት ምሥጢር በሥዕላዊ ምሳሌ ለማጠቃለል የሚከተለውን ሥዕላዊ መግለጫ እንመልከት።

# የደኅንነት ምሥጢር



የክርስትና ሕይወት ጅምር
የክርስትና ሕይወት እድገት
ከኃጢአት ውጤት መዳን (መጽደቅ)
አዲስ ፍጥረት
1
ከኃጢአት ኃይል መዳን (መቀደስ)
2
3
መቀበል
7
5
6
ኑና ውረሱ
የአገልግሎት ሽልማት
መውረስ
4
ከጌታ ጋር መኖር (የዘላለም ክብር)
የክርስትና ሕይወት ፍጻሜ

## የክርስትና ሕይወት ፍጻሜ

## የሥዕሉ መግለጫ ቁልፍ

1. ቀደም ሲል እንደ ተጠቀሰው ቁጥር አንድ የሚያሳየው ከኃጢአት ውጤት በመዳን የምናገኘው የክርስትና ሕይወት ጅምር ነው።

2. የክርስትና ሕይወት ውጤት ከኃጢአት ኃይል በመዳን በአሸናፊ ሕይወት ዕለት በዕለት ከጌታ ጋር መጓዝ ነው።

3. ከኃጢአት ውጤት በመዳንና ከኃጢአት ኃይል በመዳን መሐከል ያለውን ነው። የቁጥር ሦስት ጥሪ "ለመሆን" ነው። ከደህንነት አንጻር ስንመለከተው ጌታ የሚጠራን አዲስ ፍጥረት እንድንሆን ነው። ከክርስትና ሕይወት ዕድገት አንጻር ስንመለከት ጌታ የሚጠራን ለአሸናፊ የክርስትና ሕይወት መሆኑን እንገነዘባለን።

4. ከዚህ ሕይወት በኋላ የሚጠብቀን የዘላለም ክብር ነው።

5. ከኃጢአት ኃይል (የክርስትና ሕይወት ዕድገት) በመዳንና ለዘላለም ከጌታ ጋር በመኖር (የዘላለም ሕይወት ፍፃሜ) መካከል ያለው "የጌታ ክብር ነው።" ከክርስትና ሕይወት ዕድገት አንጻር ሲታይ ጥሪው ክብሩን ለማንጸባረቅ፤ (2ቆሮ. 3፡18)፣ ሲሆን ከደህንነታችን ፍፃሜ አንጻር ሲታይ ደግሞ ጥሪው ያዘጋጀልንን ክብር ለመውረስ ነው። (ማቴ. 25)

6. በክርስትና ሕይወት ጅማሬና ፍጻሜ (1 እና 4) መሐከል ያለው "የመቀበል" ግብዣ ነው። ከክርስትና ሕይወት ጅማሬ አንጻር (ቁጥር 1) ስንመለከተው ግብዣው ሕይወትን እንድንቀበል ነው። በሌላ አባባል ይህ የደህንነት ጥሪ ነው። ከሕይወት ፍጻሜ አንጻር ሲታይ የአገልግሎት ሽልማት የመቀበል ነገር ነው። (1ቆሮ. 3)

7. በሦስቱ (1፤ 2 እና 4) መሐከል ያለው ግኑኝነት "ኑ" የሚል ነው። ከደህንነታችን አንጻር፦ "ኑና" ዳኑ ነው። ከሕይወት ዕድገት አንጻር "ኑና" በጌታ ኑሩ ነው። ከክርስትና ሕይወት ፍጻሜ አንጻር "ኑና" ከጌታ ጋር ለዘላለም ኑሩ ነው።

"እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን።" (2ቆሮ. 3፡18)

## የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ይህ ሥዕል ምን ትርጉም ይሰጥሃል?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

2. የደህንነትን ምስጢር በሥዕል መልክ እንዴት ታስቀምጣለህ?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

3. በዚህ ሥዕል ውስጥ ሦስቱ አስፈላጊ ነገሮች ምንድን ናቸው?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

4. ጅማሬ፣ ዕድገትና ፍጻሜ አንዱ ከሌላው ጋር ያለው ተመሳስሎና ልዩነታቸው ምንድነው?

- ______
- ______
- ______
- ______
- ______

5. የቅደም ተከተላቸውን መዛባት ሊያስከትል የሚችል ችግር ያለ ይመስልሃልን?

- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________